# አረጋግጥ

## ጠቃሚ ምክሩን ይማሩ

1. **ሀሳብህ/ሽን ተናገር/ሪ፡** ልጅዎ ስለታሪኩ ያለውን/ያላትን እሳቤዎች ወይም ሀሳቦች ጠይቁ። ይህ ማንኛውም ነገር ሊሆን ይችላል፤ ይሄ ልጅ ሞኝ ነው! አይነት ሊሆን ይችላል።

2. **ከሀሳብህ/ሽ ጋር የሚመሳሰል ማስረጃ ተናገር/ሪ፡** ልጅዎን ከታሪኩ ውስጥ ምሳሌዎች በመጠቀም "እንዲያ(ድታ)ረጋግጥ" ጋብዙ/ዟት፣ እንደ፡ *ይሄ ሞኝ ልጅ ድመቷን ሊያጥባት ሞክሮ ነበር!* አይነት

3. **ከመፅሀፉ ውስጥ ሀሳብህን/ሽን የሚያረጋግጡ ምስሎች ወይም ቃላት አግኙ፡** ትናንሽ ልጆች ምስል እየጠቆሙ ማሳየት ይችላሉ፣ ትላልቅ ልጆች ደግሞ የዳሰሳ ንባብ ገፁ ላይ በማድረግ ቃላትና ሀረጎችን ማግኘት ይችላሉ።

### ይሄ ጠቃሚ ምክር ለምን አስፈለገ?

ስለ ገፀ-ባህሪያት ማሰብ እና ታሪኩ ውስጥ ስለሚፈጠሩ ነገሮች ማውራት አዝናኝ ውይይት ይፈጥራል! ሀሳባችንን የሚያጠናክር ማስረጃና ምሳሌዎች ለማግኘት ታሪኩን ደግመን ስናነብ በተሻለ መንገድ መረዳት እንችላለን።

## ልጅዎን ይጠይቁ

*ለትናንሽ ልጆች፡*

- ስለዚህ ታሪክ ምንድነው ሃሳብህ/ሽ?
- የትኛው የገፀ-ባህሪ ንግግር ወይም ድርጊት ነው ይሄንን እንድታስብ/ቢ ያደረገህ/ሽ? መቼ?
- ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነውን ምስል ጠቁም/ሚ።

*ለትላልቅ ልጆች፡*

- ይሄንን ካነበብክ/ሽ በኋላ ሀሳብህ/ሽ ምንድን ነው? አብራራ/ሪ።
- ከመፀሀፉ ይሄንን ሀሳብ ያገኘህ(ሽ)በትን ቦታ አሳየ(ይ)ኝ። ይሄ እንዴት ሀባብህን/ሽን ያረጋግጣል?
- የዚህ ታሪክ ችግር ወይም ግጭት ምን ይመስልሀል/ሻል? እነዚህን ሀሳቦች ከመፀሀፉ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የትኛው ነው?

## አዝናኝ ልምምድ

"አረጋግጥ!" ጨዋታን ተጫወቱ

- 5 አርፍተነገሮችን በአምስት የተለያዩ ወረቀቶችን ላይ ፃፉ።
- የመጀመሪያው ሰው አንድ ወረቀት ስቦ በማውጣት ጮክ ብሎ ያነባል/ታነባለች። (ለምሳሌ፡ ድመቶች ምርጥ የቤት እንስሣ ናቸው።)
- ሁለተኛው ግለሰብ ይሄ አርፍተነገር **እውነተኛ** መሆኑን የሚያሳይ ማብራሪያ ወይም ማረጋገጫ ያቀርባል/ታቀርባለች። (*ለመንከባከብ ቀላል ናቸው።*)
- ቀጥሎም የመጀመሪያው ግለሰብ አርፍተነገሩ **እውነተኛ እንዳልሆነ** የሚያሳይ ማብራሪያ ወይም ማረጋገጫ ያቀርባል/ታቀርባለች። (*አንዳንድ ሰዎች አለርጅክ ናቸው።*)
- አንደኛችሁ ማረጋገጫ ማቅረብ እስከሚያቅታችሁ ድረስ ደጋግሙት።